# ትምህርት 29

1. እስራኤላውያን በሙሴ በኩል የተነገራቸውን የእግዚአብሔር ቃል አምነዋል?

ሀ- አዎን።

2. የእግዚአብሔርን ቃል ካላመንን እግዚአብሔርን ምን እያልነው ነው?

ሀ- ውሸታም።

3. እግዚአብሔር በቃል የማያምኑትን ያድናቸዋል?

ሀ- አያድናቸውም።

4. ፈርዖን እስራኤላውያንን እንዲለቅቅ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሙሴ ሲነግረው ምን አለ?

ሀ- ፈርዖን «እግዚአብሔርን አላውቅም እስራኤልንም አልለቅም» አለ።

5. እስራኤላውያን ግብፅን ለቅቀው እንዲሄዱ ፈርዖን ንደማይፈቅድላቸው እግዚአብሔር ያውቅ ነበር?

ሀ- አዎን።

ለ- እግዚአብሔር ማናቸውንም ነገር ከመፈጸሙ አስቀድሞ ያውቃል።

6. እግዚአብሔር ለፈርዖንና ለግብፃውያን ታላቅ ኃይሉን ለማሳየት የወሰነው ለምን ነበር?

ሀ- እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ መሆኑን እንዲያውቁ ነው።

7. እግዚአብሔር ለግብፃውያንና ለእስራኤላውያን ታላቅ ኃይሉን ያሳየው እንዴት ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር ታላላቅ መቅሰፍቶችን በፈርዖንና በግብፃውያን ላይ በማውረድ ነበር።

8. እነዚያ መቅሰፍቶች ምን ምን ነበሩ?

ሀ- እግዚአብሔር ወንዙን ወደ ደም ለወጠው።

ለ- እግዚአብሔር ጓጉንቸሮች ግብፃውያንን እንዲያስጨንቁ አደረገ።

ሐ-እግዚአብሔር ትንኞች ግብፃውያንን እንዲነክሱአቸው አደረገ።

መ- እግዚአብሔር ዝንቦች ግብፃውያንን እንዲነክሱአቸው አደረገ።

ሠ- እግዚአብሔር የግብፃውያንን ከብቶች በሙሉ ገደለ።

ረ- እግዚአብሔር ግብፃውያንን በእባጭ እንዲሠቃዩ አደረገ።

ሰ- እግዚአብሔር በረዶ የግብፃውያንን እህል እንዲያጠፉ አደረገ።

ሸ- እግዚአብሔር አንበጦች የግብፃውያንን እህል እንጨርሱ አደረገ።

ቀ- እግዚአብሔር ድቅድቅ ጨለማ በመላክ ለግብፃውያን እንዳጨልም አደረገ።

9. እግዚአብሔር መቅሰፍቱን በላከ ቁጥር ሁሉ ፈርዖን ምን ይል ነበር?

ሀ- ፈርዖን ለሙሴ እስራኤላውያንን እንደሚለቅ ይነግረው ነበር።

10. እግዚአብሔር መቅሰፍቱን ባቆመ ቁጥር ፈርዖን ምን ይል ነበር?

ሀ- ፈርዖን እስራኤላውያንን አልለቅም ይል ነበር።

11. መቅሰፍቱ እስራኤላውያን ወደሚኖሩበት ክልል ያልገባው ለምንድን ነው?

ሀ- ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ እግዚአብሔር እነርሱን እንደሚባርካቸውና ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርጋቸው ቃል ገብቶ ስለነበር ነው።

12. ከእግዚአብሔር ጋር በሚታገሉት ላይ ምን ይደርስባቸዋል?

ሀ- እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል።

- እግዚአብሔር ዘጠኝ አስፈሪ መቅሰፍቶችን በፈርዖንና በግብፃውያን ላይ ቢያወርድባቸውም እንኳን ፈርዖን እሰራኤላውያንን ለቀቀን?

- አልለቀቀም።

- እግዚአብሔር ፈርዖን እስራኤላውያንን ለመልቀቅ እንደማይፈልግ ያውቅ ነበር?

- አዎን።

- ፈርዖን እስራኤላውያንን ለመልቀቅ እንደማይፈልግ እግዚአብሔር መቼም ያውቅ ነበር።

- እግዚአብሔር ሙሴ እስራኤላውያንን እንዲመራ ከመጥራቱ አስቀድሞ እንኳን ፈርዖን እስራኤልን እንደማይለቅ ያውቅ ነበር።

- እግዚአብሔር ሁሉም ነገር ከመፈጸሙ በፊት ያውቃል።

- ፈርዖን ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ማሸነፍ ይችላል?

- አይችልም።

- ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ማሸነፍ የሚችል ሰው አለ?

- የለም።

- ሰዎች የፈለጉትን ቢናገሩም እንኳን የእግዚአብሔርን ሥራ ማስቆም አይችሉም።

- ሰዎች የፈለጉትን ቢያደርጉም የእግዚአብሔርን ሥራ ማስቆም አይችሉም።

- እግዚአብሔር አንድን ነገር ለማድረግ ከወሰነ ምንጊዜም ይፈጽመዋል።

- እግዚአብሔር አንድ ተጨማሪ መቅሰፍት ይልክና ያን ጊዜ ፈርዖን እስራኤላውያንን ይለቅቃል።

ዘጸአት 11፡1

1- እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ «በፈርዖንና በግብፅ ላይ አንድ ሌላ መቅሰፍት አወርድባቸዋለሁ፤ ከዚያም በኋላ፣ ፈርዖን ይለቅቃችኋል፤ ሲለቃችሁም አንዳችሁን ሳያስቀር ያስወጣችኋል።»

- እግዚአብሔር የሚልከው የመጨረሻ መቅሰፍት ምን ነበር?

ዘጸአት 11፡4-7

4- ከዚህ በኋላ ሙሴ እንደህ አለ፤ «እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፤ እኩለ ሌሊት ሲሆን በመላው የግብፅ ምድር ላይ አልፋለሁ።

5- በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ከፈርዖን ልጅ አንሥቶ የወፍጮ መጅ ገፊ እስከ ሆነችው እስከ ባሪያይቱ ልጅ ድረስ በግብፅ ምድር በኩር ሆኖ የተወለደ ወንድ ልጅ ሁሉ ይሞታል። እንዲሁም የቀንድ ከብቱ በኩር በሙሉ ያልቃል።

6- በግብፅ ምድር ሁሉ ከዚህ በፊት ያልተሰማ ወደፊትም የማይሰማ ታላቅ ዋይታ ይሆናል።

7- በእስራኤላውያን ዘንድ ግን በሰውም ሆነ በእንስሳት ላይ ውሻ እንኳ አይጮኽባቸውም። በዚህም እግዚአብሔር በግብፃውያንና በእስራኤላውያን መካከል ልዩነት የሚያደርግ መሆኑን ታውቃላችሁ።

- እግዚአብሔር የሚልከው የመጨረሻው መቅሰፍት የግብፃውያንን ልጆችና ከብቶች በኩር የሚገድል ነበር።

- የመጨረሻው መቅሰፍት አስፈሪ ስለ ነበር እግዚአብሔር እስራኤላውያን ለመጨረሻው መቅሰፍት እንዲዘጋጁ ነገራቸው።

- የመጨረሻው መቅሰፍት እጅግ አስፈሪ ስለ ነበር የእስራኤላውያን በኩር ወንዶች እንዳይሞቱ እስራኤላውያን ምን እንዲያደርጉ እግዚአብሔር አዘዛቸው?

ዘጸአት 12፡1 & 3-5

1- «እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን በግብፅ እንዲህ አላቸው፤

3- ለመላው የእስራኤል ሕዝብ ይህንን ንገሩ፤ ይህ ወር በገባ በአሥረኛው ቀን እያንዳንዱ ሰው አንዳንድ ጠቦት ለቤተሰቡ፣ አንዳንድ ጠቦት ለአባቱ ቤት ያዘጋጅ።

4- ማንኛውም ቤተሰብ ለአንድ ሙሉ ጠቦት ቁጥሩ አነስተኛ ከሆነ፣ በጐረቤት ያሉትን ሰዎች ቁጥር እስከ ቅርብ ከሆነው ጋር መካፈል ይኖርበታል፤ እያንዳንዱ ሰው በሚበላው መጠን ምን ያህል ጠቦት እንደሚያስፈልግ መወሰን ይኖርባችኋል።

5- የምትመርጡት ጠቦት በግ ወይም ፍየል ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ምንም ነውር የሌለበትና አንድ ዓመት የሞላው ተባዕት (ወንድ) መሆን አለበት።»

- እያንዳንዱ የእስራኤላውያን ቤተሰብ ባል የበኩር ልጁ እንዳይሞት ምን እንዲያደርግ እግዚአብሔር አዘዘው?

- የአንድ ዓመት የበግ ወይም የፍየል ጠቦት እንዲመርጥ።

- የእስራኤላውያን እንዲመርጡ እግዚአብሔር ያዘዘው በግ ወይም ፍየል ምን አይነት ነበር?

- ምንም ነውር የሌለበት።

- ለምንድን ነው እግዚአብሔር ነውር የሌለበት የአንድ ዓመት የበግ ወይም የፍየል ጠቦት እንዲያዘጋጁ ያዘዘው?

- እግዚአብሔር ፍጹም ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር የሚናናገረው ነገር ሁሉ ፍጹም ስለሆነ ነው።
- እግዚአብሔር አሚያደረገው ነገር ሁሉ ፍጹም ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር የሚቀበለው ነውር የሌለበትን የአንድ ዓመት የበግ ወይም የፍየል ጠቦት ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር ፈጽሞ በሽተኛ መሥዋዕት አይቀበልም።
- እግዚአብሔር ፈጽሞ የተጎዳ መሥዋዕት አይቀበልም።

- በይስሐቅ ፈንታ ሊሠዋ ቀንዶቹ በቁጥቋጦ ውስጥ ተይዞ የነበረውን አውራ በግ ታስታውሳላችሁ?

- ያ አውራው በግ በቀንዶቹ የተያዘው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍጹም ስለሆነ ነው።
- እግዚአብሔር የሚቀበለው ፍጹም መሥዋዕት ብቻ ነው።

- እስራኤላውያን ከሞት እንዲድኑ በጥንቃቄ ማድረግ ያለባቸው ነገር ምን ነበር?

- እግዚአብሔርን መታዘዝ።
- ነውር ከሌለበት በግ ወይም ፍየል የአንድ ዓመቱን ጠቦት ብቻ መምረጥ።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ቀጥሎ ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

ዘጸአት 12፥6

6- ወሩ በገባ እስከ አሥራ አራተኛው ቀን ድረስ ጠብቋቸው፤ በዚያ ምሽት ጀምበር ስትጠልቅ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ይረዱአቸው።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን ጠቦቱን እስከ ስንተኛው ቀን ድረስ እንዲጠብቁ አዘዛቸው?

- በወሩ እስከ አሥራ አራተኛው ቀን ድረስ።

- እግዚአብሔር በወሩ በአሥራ አራተኛው ቀን ጠቦቱን ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው።

- እግዚአብሔር ጠቦቱ እንዲታረድ አዘዛቸው።

- እግዚአብሔር ጠቦቱ እንዲሞት አዘዛቸው።

- እግዚአብሔር ጠቦቱ እንዲሞት ያዘዘው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚቀጣው በሞት መሆኑን ለእስራኤላውያን ለማስተማር ነው።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአት ከመሥራታቸው በፊት በዓለም ላይ ሞት አልነበረም።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአት ስለ ሠሩ ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአት ስለ ሠሩ ሞት በሰዎች ሁሉ ላይ መጣ።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን የጠቦቱንም ደም ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

- በጎድጓዳ ሳሕን ውስጥ እንዲያስቀምጡት አዘዛቸው።

- እስራኤላውያን ከሞት እንዲድኑ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በጥንቃቄ መጠበቅ አለባቸው።

- ነውር የሌለበትን የአንድ ዓመት የበግ ወይም የፍየል ጠቦት አርደው ደሙን በጐድጓዳ ሳሕን ውስጥ ማኖር አለባቸው።

- ከዚያስ እግዚአብሔር እስራኤላውያን በጎድጓዳ ሳሕን ውስጥ ያለውን ደም ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

ዘጸአት 12፡7

7- ከዚያም ከደሙ ወስደው የጠቦቶቹ ሥጋ የሚበላበትን የእያንዳንዱን ቤት ደጃፍ መቃንና ጉበን ይቀቡ።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በዚያ ምሽት የበጉን ሥጋ የሚበሉበትን ቤት ሁለቱን መቃንና ጉበን እንዲቀቡ አዘዛቸው።

- እስራኤላውያንን ከእግዚአብሔር ቅጣት የሚያድናቸው የጠቦቱ ደም ነበር።

- እስራኤላውያን ከሞት እንዲድኑ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በጥንቃቄ መጠበቅ አለባቸው።

- እንዲሁም የበጉን ሥጋ በሚበሉበት ምሽት የጠቦቱን ደም በቤታቸው መቃንና ጉበን መቀባት አለባቸው።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ያዘዘው ሌላ ትእዛዝ ምን ነበር?

ዘጸአት 12፥22ለ

22- እግዚአብሔርም እንዲህ አለ «ከእናንተ አንድም ሰው እስኪነጋ ድረስ ከቤቱ አይውጣ።»

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን እስኪነጋ ድረስ ደሙ በተቀባበት ቤት ውስጥ እንዲቆዩ አዘዛቸው።

- እስራኤላውያን ከውጭ ደም በተቀባ ቤት ውስጥ መቆየት ነበረባቸው።

- እስራኤላውያን ከውጭ ደም በተቀባ ቤት ውስጥ መቆየት የነበረባቸው ለምንድን ነው?

- በውጭ ያለው ደም በውስጥ ያሉትን እስራኤላውያን ስለሚሸፍን ነው።

- በውጭ በጉ የሞተው በውስጥ ያሉትን እስራኤላውያንን ለመሸፈን ነው።

- እስራኤላውያን ከሞት እንዲድኑ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በጥንቃቄ መጠበቅ አለባቸው።

- በሩ በደም በተቀባ ቤት ውስጥ እስኪነጋ ድረስ መቆየት አለባቸው።

- በመቀጠል እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ያዘዛቸው ሌላ ትዕዛዝ ምንድን ነው?

ዘጸአት 12፡46ለ

46- እግዚአብሔር፤ «ምንም አጥንት እንዳትሰብሩ» አለ።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን የጠቦቱን አጥንት እንዳይሰብሩ አዘዛቸቸው።

- እስራኤላውያን ከሞት እንዲድኑ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በጥንቃቄ መጠበቅ አለባቸው።

- የበጉን ወይም የፍየሉን ጠቦት አጥንት በፍጹም መስበር አይኖርባቸውም።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን ሁሉንም ነገር ልክ ባዘዛቸው መሠረት እንዲያደርጉ ነገራቸው።

- እስራኤላውያን ሁሉንም ነገር እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት ባያደርጉ ምን ይደርስባቸዋል?

- መቅሰፍቱ በእነርሱም ላይ ይመጣና የበኩር ልጆቻቸው ይሞታሉ።

- እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን የበኩር ልጆች የሚያድነው ሁሉንም ነገር ልክ እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት የሚያደርጉ ከሆነ ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን የበኩር ልጆች ከሞት የሚያድነው እነርሱ የእግዚአብሔርን መንገድ ከተከተሉ ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር እኛ በራሳችን መንገድ ራሳችንን እንድናድን ይፈቅዳል?
- አይፈቅድም።

- ሊያድነን የሚችለው ብቸኛ መንገድ የማን መንገድ ነው?
- የእግዚአብሔር መንገድ ነው።

- አዳምና ሔዋን የራሳቸውን መንገድ በመከተል የቅጠል ልብስ ለራሳቸው ባዘጋጁ ጊዜ ምን ሆነ?

- እግዚአብሔር የቅጠል ልብሳቸውን አልቀበልም አለ።

- ቃየን እግዚአብሔር በተናገረው መንገድ መሥዋት ማቅረብ እምቢ ብሎ የራሱን መንገድ በመከተሉ ምን ሆነ?

- እግዚአብሐር የቃየንን መሥዋዕት አልቀበልም አለ።
- ሊያድነን የሚችለው የእግዚአብሔር መንገድ ብቻ ነው።

- በእግዚአብሔር መንገድ የማንሄድ ከሆነ እግዚአብሔር አይቀበለንም።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን የሚታዘዙት ከሆነ ምን እንደሚያደርግ ቃል ገባ?

ዘጸአት 12፥12-14

12- እግዚአብሔርም እንዲህ አለ «እኔም በዚያች ሌሊት በግብፅ ምድር ላይ አልፋለሁ፤ ከሰውም ከእንስሳም የተወለደውን የበኵር ልጅ ሁሉ እገድላለሁ። የግብፅን አማልክት ሁሉ እፈርድባቸዋለሁ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤

13- ደሙም ያላችሁበትን ቤት ለይቶ የሚያሳይ ምልክት ይሆንላችኋል፣ እኔ ደሙን በማይበት ጊዜ፣ እናንተን አልፋለሁ፤ ግብፅን ስቀጣ፣ መቅሰፍቱ አይደርስባችሁም።

14- ይህን ቀን መታሰቢያ ታደርጉታላችሁ። በሚቀጥሉት ትውልዶች ሁሉ ቋሚ ሥርዓት ሆኖ የእግዚአብሔር በዓል አድርጋችሁ ታከብሩታላችሁ።»

- እስራኤላውያን የሚታዘዙት ከሆነ እግዚአብሔር ምን ብሎ ቃል ገባ?

- እግዚአብሔር መቅሰፍቱ እንደማያገኛቸውና የበኩር ልጆቻቸው እንደማይሞቱ ቃል ገባ።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ታዘው ነበር?

ዘጸአት 12፡28

28- እስራኤላውያንም እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዳዘዛቸው አደረጉ።

- እስራኤላውያን ልክ እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ።

- አንድ እስራኤላዊ ሕመምተኛ ጠቦት መርጦ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ያድነው ነበር?

- አያድነውም።

- አንድ እስራኤላዊ ጠቦቱን ሳያርደው በበሩ አጠገብ ብቻ አስሮት ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ያድነው ነበር?

- አያድነውም።

- ጠቦቱ መሞት ነበረበት።

- የጠቦቱ ደም መፍሰስ ነበረበት።

- እግዚአብሔር የኃጢአት ቅጣት ሞት እንደሆነ እስራኤላውያን እንዲረሱ አልፈለገም።

- በዚያ ሌሊት ምን ሆነ?

ዘጸአት 12፥29-30

29- እኩለ ለሊት ላይ እግዚአብሔር በግብፅ ምድር በዙፋን ላይ ከተቀመጠው ከፈርዖን የበኵር ልጅ ጀምሮ በጨለማ እሥር ቤት ውስጥ እስካለው እስረኛ የበኵር ልጅ ድረስ ያለውንና የእንስሳቱን በኵሮች ሁሉ ቀሠፋቸው።

30- ፈርዖን፣ ሹማምንቱና የግብፅ ሕዝብ በሙሉ ሌሊቱን ከመኝታቸው ተነሡ፤ እነሆ በመላይቱ ግብፅ ለቅሶና ዋይታ ነበር፤ ሰው ያልሞተበት አንድም ቤት አልነበረምና።

- የፈርዖን የበኵር ልጅና የመላው ግብፃዊ የበኵር ልጆች ሞቱ።

- የፈርዖን ከብቶች በኵሮችና የግብፃውያን ከብቶች በኵሮች ሁሉ ሞቱ።

- እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት የግብፃውያንን በኵሮች ሁሉ ገደለ?

- አዎን።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚቀጣው በሞት ነው።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ ይቀጣል።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት ይቀጣል።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ለመቅጣት በሚወስንበት ጊዜ ማንም ሊያመልጥ አይችልም።

- ከእስራኤላውያን በኵራት የሞተ ነበር?
- አልነበረም።

- ከእስራኤላውያን አንድም በኵር ያልሞተው ለምን ነበር?

- እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በመታዘዝ በቤቶቻቸው በሮች ላይ ደም ስለ ቀቡ ነው።

- በይስሐቅ ምትክ ነውር የሌለበት አውራ በግ እንደ ሞተ ሁሉ ነውር የሌሉባቸው ጠቦቶች በእስራኤላውያን በኵራት ምትክ ሞቱ።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ስለ ታዘዙ እግዚአብሔር ቃሉን በመጠበቅ የእስራኤላውያንን ቤቶች አለፈ?

- አዎን።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት አውጥቶ እንደሚመራቸው የገባውን ቃል አስታወሰ።

- እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከእስራኤላውያን አዳኝ እንደሚልክ የገባውን ቃል አስታወሰ።

- እስራኤላውያን እንደ ግብፃውያን ሁሉ የአዳምና የሔዋን ልጆች ናቸው።

- እስራኤላውያን እንደ ግብፃውያን ሁሉ በኃጢአት ተወልደዋል።

- እስራኤላውያን ኃጢአትን ስለ ሠሩ እንደ ግብፃውያን ሁሉ ሞት ይገባቸው ነበር።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ያዳናቸው ከእርሱ ጸጋ የተነሣ ብቻ ነው።

- ማንም ሰው የሚድነው ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ብቻ ነው።

- ከፈርዖንና ከግብፃውያን በኵራት ሞት በኋላ ፈርዖን ምን አደረገ?

ዘጸአት 12፡31-36

31- ፈርዖን ሙሴንና አሮንን ሌሊቱን አስጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ «ተነሡ፣ እናንተና እስራኤላውያን ከሕዝቤ መካከል ውጡ! ሂዱ፣ በጠየቃችሁት መሠረት እግዚአብሔርን አምልኩ፤

32- እንዳላችሁት የበግና የፍየል መንጋችሁን፣ የቀንድና የጋማ ከብቶቻችሁን ይዛችሁ ሂዱ፤ እኔንም ባርኩኝ።»

33- ግብፃውያን አገራቸውን በአስቸኳይ ለቅቀው እንዲወጡላቸው እስራኤላውያንን አጣደፏቸው። «አለበለዚያማ ሁላችንም ማለቃችን ነው» አሉ።

34- ስለዚህ ሕዝቡ ያልቦካውን ሊጥ በየቡሆ ዕቃው አድርገው በጨርቅ ጠቅልለው በትከሻቸው ተሸከሙ።

35- እስራኤላውያን ሙሴ እንዳዘዛቸው የብርና የወርቅ ዕቃዎች እንደዚሁም ልብስ እንዲሰጧቸው ግብፃውያኑን ጠየቋቸው።

36- እግዚአብሔር በግብፃውያን ፊት ለእስራኤላውያን ሞገስ ስለ ሰጣቸው፣ የጠየቋቸውን ሁሉ ሰጧቸው፣ ስለዚህ የግብፃውያንን ንብረት በዝብዘው ወሰዱ።

- በዚያ ምሽት ፈርዖን ሙሴን ጠርቶ እስራኤላውያን እንዲሄዱ ፈቀደ።

- ፈርዖን ከእግዚአብሔር ጋር መታገል እንደሚችል መስሎት ነበር።
- ፈርዖን ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ የሚያሸንፈው መስሎት ነበር።

- ደግሞም ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ የሚያሸንፈው መስሎት ነበር።

- ማንም እግዚአብሔርን ማሸነፍ አይችልም።

- ማንም የእግዚአብሔርን ሥራ ማስቆም አይችልም።

- እግዚአብሔር በእርሱ መንገድ የሚጓዙትን ያድናቸዋል።

- እግዚአብሔር በራሳቸው መንገድ የሚጓዙትን ያጠፋቸዋል።

ዘጸአት 12፥51

51- በዚያች ዕለት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በየሠራዊታቸው አድርጎ ከግብፅ ምድር አወጣቸው።

- እግዚአብሔር ቃሉን በመጠበቅ እስራኤላውያንን መርቶ ከግብፅ ምድር አወጣቸው።

- ፈርዖን ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ማሸነፍ ችሏል?
- አልቻለም።

- ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ማሸነፍ የሚችል አለ?
- የለም።